# ሌላው ከእሳቱ ውስጥ አውጡኝ ሲል እኛ ለመግባት ስንጣደፍ!

## ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል መሆን የለባትም !!

### መግቢያ

ከዚህ ቀደም ባወጣኋቸው ሁለት ጽሁፎቼ ፣ ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት(WTO)አባል ብትሆን ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝንና እንደ ህብረተሰብም ልትገነባ እንደማትችል በቲዎሪም ሆነ በተግባር(empirical) ለማሳየት ሞክሬያለሁ። በተለይም በእንግሊዘኛ ቋንቋ ባወጣሁት ጽሁፌ ፣ አገዛዙ ተገዶም ሆነ ፈቅዶ በዓለም ባንክና በዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅት(IMF) የመዋቅር ማስተካከያ ፕሮግራም (Structural Adjustment Program) ተግባራዊ በማድረጉ በነጻ ገበያ ስም የተካሄደው ፖሊሲ የአገራችንን ኢኮኖሚ ወደ ፊት እንዳላረመደው ለማረጋገጥ ሞክሬያለሁ። በነጻ ገበያ ፖሊሲ የተነሳ ወደ ውስጥ ያተኮረና ጠቅላላውን ህብረተሰብ ያካተተ ኢኮኖሚ የተገነባ ሳይሆን ፣ ጥቂቱን የህብረተሰብ ክፍል የጠቀመና አባዛኛውን ደግሞ ወደ ድህነት የገፈተረ ኢኮኖሚያዊ አወቃቀር ተዘርግቶ ህብረተሰብአዊ ትርምስ እንደተፈጠረ ከጽሁፉ መገንዘብ ይቻላል።

በተለይም አንባብያን የጸሁፌን ሎጂካዊ አቀራረብ እንዲረዱና እንዲያምኑ የነጻ ንግድ ፖሊሲ በምን ጊዜና ከማን ጥቅም አንጻር እንደፈለቀና ለምንስ በ18ኛውና በ19ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩ ምሁራን እንደተቃወሙት ለማመልከት ሞክሬያለሁ። በመሆኑም ለአንድ አገር ዕድገትና ህብረተሰብኢዊ ትስስር ፣ ባህልና ሌሎች መንፈሳዊ ነገሮች እንዲዳብሩ ከተፈለገ የነጻ ገበያና ዓለም አቀፋዊ ንግድ ሳይሆኑ የዕድገት መሰረቱ ፣ የግዴታ በሳይንስና በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ሁለንታዊና ሰፊውን ህዝብ የሚያሳትፍ ፖሊሲ መንደፍ አስፈላጊ መሆኑን በተለይም የጀርመንና የአንዳንድ ምዕራብ አውሮፓውያን አገሮችን ልምድ በመጥቀስ ጽሁፌን አስምሬበታለሁ። ስለሆነም የአንድ አገር ህዝብ ብሄራዊ ስሜቱ ሊዳብርና እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ህብረተሰብ ነጻነት ሊሰማው የሚችለው ከውጭ በመጣ ፖሊሲና ድንጋጌ መሰረት ሳይሆን ፣ ከአገሪቱ የፈለቁ ምሁራንና ህዝቡ የሚሳተፍበት ፖሊሲ ሲነደፍ ብቻ መሆኑን ማመልከት ተችሏል።

ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ለመሆን ካመለከተች ከአምስት አመት በላይ ሆኗል። በድርጅቱ የአሰራር ደንብ መሰረትም ሆነ አገሪቱ ማሟላት ያለባት ነገሮች ስላሉ ድርድሩ እስካሁን ሊጓተት ችሏል። በተለይም የኢህአዴግ አገዛዝ የአገልግሎት መስኩን ፣ እንደ ባንኩንና የቴሌኮሙኒኬሽኑን የመሳሰሉትን ወደ ግል ሀብትነት አላዞርም በማለቱ ድርድሩ እንዲራዘምና መቋጠሪያ እንዳያገኝ አድርጎታል። ይህም ሆኖ ግን ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊና የንግድና የኢንዱስትሪ ሚኒስተሩ አቶ ግርማ ኢትዮጵያ የግዴታ የድርጅቱ አባል እስክትሆን ድረስ ውትወታችንን አናቆምም ብለዋል።

ይህ የእነ አቶ መለስ ጭቅጨቃ አሁን የዓለም ንግድም ሆነ የዓለም ኢኮኖሚ በከፍተኛ ደረጃ በተዛባበትና ፣ በተለይም ደግሞ የሶስተኛው ዓለም አገሮች ወደ ኢንዱስትሪ አገሮች የሚልኩት ምርትና የጥሬ ሀብት እየቀዘቀዘ በመጣበት ወቅት ነው። በተጨማሪም ብዙ የኢንዱስትሪ አገሮች ከዚህ ቀደም በብዛት ያመረቱትን ምርት ወደ ውስጥም ሆነ ወደ ውጭ ለመሸጥ ያልቻሉበት ሁኔታ በተፈጠረበት ጊዜ ነው። በዚህም ምክንያት በአንድ በኩል ክፉኛ እየተዳከመ የመጣውን የውስጥ ገበያ ለማንቀሳቀስና በተለይም ደግሞ ኢንዱስተሪዎችንና ባንኮችን ለመደጎም አዳዲስ ስትራቴጂዎች በሚቀይሱበት ወቅት ነው። ስለሆነም እንደ ፈረንሳይ ያሉ አገሮች ወደ እገዳ ፖሊሲ ሊያመሩ ይችላሉ ተብሎ በሚፈራበት ወቅትና የፖለቲካ መቃቃርም ቀስ በቀስ በሚታይበት ጊዜ  የግዴታ የዓለም ንግድ ድርጀት አባል ካልሆንኩ ታንቄ እሞታለሁ ማለት በዕውነቱ የዓለምን ኢኮኖሚ የወደፊት ጉዞ ለመረዳት አለመቻል ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን ፣ አገዛዙ ቀደም ብለው የደርጅቱ አባል ከሆኑ አገሮችና ያገኙትን ጥቅምና የደረሱበትን የዕድገት

ደረጃ ማጤን ነበረበት። እንደሚታወቀው ደካማ አገሮች አባል በመሆናቸው ውስጣዊ የኢኮኖሚ ጥንካሬ እንዳለገኙ ይታወቃል። በተለይም ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ ገበያቸውን ልቅ ያደረጉ አገሮችና የአውሮፓ የጋራ ገበያ አባል የሆኑ ወደ ውስጥ ያተኮረ የኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ባለማትኮራቸው ብዙዎቹ ወደ መከስከስ እያመሩ እንደሆን ሁኔታዎችን ለሚከታተል ሊገነዘብ ይችላል። ወደ ዋናው የነጻ ገበያና ንግድ አራማጅ ወደ ሆነው አሜሪካ ስንመጣ ፣ ከምርጫው ጀምሮ የተካሄደው ክርክርና ውይይት የሚያረጋግጠው ፣ ልቅ የነጻ ገበያ  ኢኮኖሚውን ክፉኛ እንደ ጎዳው ነው። ስለሆነም ፕሬዚደንት ኦባማ ስልጣኑን ከተረከቡና የኢኮኖሚ አንቀሳቃሽ ፕሮግራም(Stimulus packet) ከተነደፈ ወዲህ በፖሊሲው ውስጥ የተካተተው አረፍተ ነገር(clause) በመጀመሪያ ደረጃ የአሜሪካን ዕቃ መግዛት (buy America) አለበት የሚል ነው። ወደ ዓለም ንግድ ድርጅቱ ስንመጣ ፣ እ.አ በ2001 ዓ.ም በዶሀ ላይ የተደረሰበት ንግድንና ዕድገትን ያካተተ ፖሊሲ እስካሁን ስምምነት ያልተደረሰበትና ወደፊትም ካለምንም ውጤት እንደሚቋረጥ የታመነበት ፣ ሁኔታው ለሶስተኛው ዓለም አገሮች አመቺ አለመሆኑን ነው ያሚያረጋግጠው። የኢንዱስትሪ አገሮች ለእርሻ ድጎማ የሚሰጡትን ከተወሰነ ፐርሰንት በታች ለመቀነስ ፈቃደኛ ባለመሆናቸውና አባል የሆኑት የሶስተኛው ዓለም አገሮችም በኢንዱስትሪ አገሮች ግትርነት ፣ በተለይም ትንሽ  የልብ ልብ የተሰማቸው እንደ ህንድና ብራዚል የመሳሰሉት በውይይቱ ለመግፋት ፈቃደኛ ባልሆኑበት ወቅት ፣ በዚህ ዐይነት ሁኔታ ውስጥ ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ካልሆነች ታንቄ እሞታለሁ ብሎ መከራከሩ ለምን ይጠቅማል ? በእርግጥስ አባል የመሆን ዕድል ብታገኝ አገዛዙ እንደሚያምንበት አገራችን የእርሻ ምርቷን እንደ ልብ በዓለም ገበያ ላይ ማራገፍ ትችላለች ወይ ? በጣም የሚያጠራጥር ጉዳ ነው።

የመዋቅር ማስተካከያ ፖሊሲ በአገራችን ላይ ያመጣውን መዘዝ ፣ ኢኮኖሚያዊ ድቀትና የባህል መከስከስ ፣ በተለይም ደግሞ የአቶ መለስ አገዛዝ ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል እንድትሆን ካመለከተ ወዲህ በተቃዋሚው ዘንድ ይህን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫም ሆነ ሀተታ የለም። እንዲያውም ይባስ ብሎ የዓለም ንግድ ድርጅቱ ጠበቃ ያሚያስመስል ከግንቦት ሰባት መሪዎች በኒውስ ሌተራቸው ላይ ወጥቷል። መግለጫውም የሚለው ፣ የባንኩንና የቴሌኮሙኒኬሽኑን ዘርፍ የዓለም ንግድ ድርጅቱ በሚፈልገው መልክ  የእነ አቶ መለስ መንግስት ወደ ግል ሀብትነት ለማዞር ፈቃደኛ አይደለም የሚል የውንጀላ አቀራረብ ነው። እዚህ ላይ እነ አቶ መለስ የሚያካሂዱትን አገር አፍራሽ ተግባርና የተበላሸ ኢኮኖሚ ፖሊሲ መኮነና የእነሱን እምቢተኝነት ነጣጥሎ ማየት የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ነገ የአቶ መለስ መንግስት ከአሜሪካ ጋር ያለውን የጠበቀ ግኙኝነት አቀዘቀዘኩ ቢል እሰይ ከማለት ይልቅ ልንወነጅለው ነው ማለት ነው ? የግንቦት ሰባት መሪዎች በተለይም በዓለም ንግድ ፣ በዓለም ባንክና በዓለም የገንዘብ ድርጅት የሚካሄደውን የተቀነባበረ የድህነት ፖሊሲ በደንብ የመረመሩ አይመስልም። ከአስር ዓመት በላይ በጦቢያ መጽሄትና በሌሎች ጋዜጦችም ሆነ መጽሄቶች ላይ ይወጣ የነበረውን ቃለ መጠይቅም ሆነ ገለጻ ስንመለከት የተቃወሚው ቡድን በአገዛዙና በውጭው ኃይል መሀከል ያለውን መተሳሰር የተገነዘበ አይመስልም። በዚህም ምክንያት ብሄራዊ ነፃነታችን እንደተረገጠና ለውርደት እንደበቃን ግንዛቤ ውስጥ የተገባ አይመስልም።

ከአገራችን ጠቅላላ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴም ሆነ በአሁኑ ወቅት በመንገዳገድ ላይ የሚገኘውን በካፒታሊሰት አገሮች የሚመራውን ዓለም አቀፋዊ ኢኮኖሚ አወቃቀር ስንመለከት ፣ የአገራቸን የዓለም ንግድ ድርጅት አባል መሆን አሁንም ቢሆን ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝን ማጤን ያስፈልጋል። አሉታዊ ጎኑን ለማረጋገጥ ወደ ታች አጠር አጠር ባለ መልክ ለማተት እሞክራለሁ።

## የተሳሳተ ቲዎሪ ፣ የተሳሳተ አመለካከት !

በመጀመሪያ ደረጃ የነጻ ንግድንና ገበያን በሚመለከት የአቶ መለሰ አገዛዝም ሆነ የተቃሚው ኃይል መገንዘብ ያለባቸው ነገሮች አሉ። 1ኛ) በታሪክ ውስጥ የነጻ ገበያን መመሪያ በማድረግ እንደ ህብረተሰብ የተመሰረተ ፣ የተገነባና ያደገ አገር በፍጹም የለም። 2ኛ) በ18ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻና በ19ኛው ክፍለ ዘመን የነጻ ንግድንና ልቅ ገበያን የተቃወሙት ምሁራን ፣ ልጆች ፣ አናርኪስቶች ወይም ጥራዝ ነጠቆች ሳይሆኑ ፣

በከፍተኛ ዕውቀት የተካኑ ፣ የሰውን ልጅ ታሪካዊ ሰሪነት የተረዱና አንድ ህብረተሰብ በምንስ መልክ ቢደራጅ ሰላምንና ብልጽግናን ሊጎናጸፍ ይችላል ብለው ቀን ሌለት የሚመራመሩ ምሁራን ነበሩ። ዛሬም ቢሆን የዓለም አቀፍ ያልተስተካከለ ኢኮኖሚያዊ አወቃቀር የሚያሳስባቸው ምሁራን የሚያነሱት ጥያቄና መከራከሪያ ነጥቦች ፣ ሁኔታው በዚህ መልክ ሊቀጥል እንደማይችል በመረዳታቸው ነው። በተለይም በሶስተኛው ዓለም አገሮች ላይ የሚደረገው ተጽዕኖና የጥሬ ሀብታቸው መበዝበዝና ጦርነት ከምዕራቡ የካፒታሊዝም መስፋፋትና በየአገሮቹ እየገቡ መፍትፌት ተነጥሎ መታየት እንደሌለበት አጥብቀው ያሳስባሉ። ስለዚህም እነዚህም ምሁራን እንደቀድሞዎቹ በከፍተኛ ዕውቀት የተካኑና ለዕውነተኛው ስልጣኔ ተቆርቋሪ በመሆናቸው እንጂ ፣ አንዳንዶቹ ሊያሳምኑን እንደሚሞክሩት ዕብዶች ሰለሆኑ አይደለም። ከዚህ ስንነሳ የዓለምን ሁኔታና የዕውቀት ፈለግ ጠጋ ብሎ ለተመለከተ ፣ ድሮም ሆነ ዛሬ የሚካሄደውን በከፍተኛ ፍልስፍና የሚደገፈውን የኢኮኖሚና የስልጣኔ አቅጣጫ እንዳልሰማ ሆኖ ዝም ብሎ ማለፍና በሚሊዮን የሚቆጠርን ህዝብ በሚያሳሳት መፌክርና ፖሊሲ ላይ መረባረብ ትልቅ የታሪክ ወንጀል እንደ መስራት መቆጠሩ መታወቅ አለበት። የእነ አቶ መለስን የእልክ ጉዞ ትተን በተለይም ተቃዋሚ ነኝ የሚለው ኃይል የኢትዮጵያን ህዝቦች ኑሮ መሻሻልና የአገራችንን አጠቃላይ ዕድገት የሚሻ ከሆነ ዝም ብሎ መተኛት የለበትም። የአስተሳሰብ ስልቱን መቀየር ብቻ ሳይሆን አስራ ስምንት ዐመት በአገራችን ምድር ተግባራዊ የሆነው የኢኮኖሚ ፖሊሲ ያመጣውን ጠንቅና በስተጀርባው ያለውን ፍልስፍና እየተነተነ ማቅረብ መቻል አለበት። የዛሬውንና መጭውን ትውልድ ለማስተማር ቆርጦ መነሳት አለበት። ይህንን ሲያደርግ ብቻ ከኢትዮጵያ ህዝቦች ጎን የቆመ መሆኑን ለማረጋገጥ ይችላል።

እንደሚታወቀው በአጠቃላይ የኢኮኖሚ ቲዎሪም ሆነ በተለይ ደግሞ የነጻ ንግድ እንደ ተፈጥሮ ሳይንስ ሳይሆኑ በተወሰነ የአስተሳሰብ ስልት የተነደፉና ከተወሰነ የህብረተሰብ ክፍል ጥቅም አንጻር ተቀነባብረው የወጡ ናቸው። ለዚህም ነው ኢኮኖሚክስ ትችታዊ አመለካከት ባላቸው ምሁራን ጨለማው ሳይንስ (Dismal Science) በመባል የሚታወቀው። ጠለቅ ያለውን ቲዎሪ ልተውና ወደ ነጻ ንግድና ዓለም አቀፋዊ የስራ ክፍፍል ስንመጣ ፣ ከ18ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የተካሄደው ክርክር የሚያረጋግጠው ቲዎሪው በጊዜው ኃያል ከነበረቸው እንግሊዝ ጥቅም አንጻር የነደፈ መሆኑን ነው። ደጋግሜ ለማሳየት እንደሞከርኩትና በሺህ በሚቆጠሩ ሊትሬቸሮች እንደተረጋገጠው ፣ እንግሊዝ የበላይነቷን ለማረጋገጥ ስትል የግዴታ የነጻ ንግድንና ገበያን የየአገሮች ዕድገት መመሪያ እንዲሆን ለማድረግ በቃች። የኢኮኖሚ ቲዎሪ ዝም ብሎ የፈለቀ ሳይሆን ከአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በክስተት ላይ የተመሰረተው እነ ጆን ሎክና ሆበስ የሚያራምዱት ፍልስፍና የበላይነቱን እየተቀዳጀ ከመጣ ወዲህ ነው። ስለሆነም የነጻ ንግድና ገበያ መመሪያ በዚህ በክስተት ላይ በተመሰረተ ፍልስፍና በመደገፍ ቀስ በቀስ የበላይነቱን ሊቀዳጅ ችሏል። በቲዎሪው መሰረትም ፣ በአገሮች መሀከል የስራ ክፍፍል መኖር አለበት። ሁሉም አገሮች ሁሉንም ነገር ማምረት ስለማይችሉና በተፈጥሮም ሆነ በሌላ ምክንያት ሁሉም የጥሬ ሀብት ፣ ካፒታል ፣ የሰው ኃይልና መሬት በሁሉም አገሮች ተሟልተው ስለማይገኙ ፣ እንደመጠኑ በዓለም ገበያ ላይ የሚሳተፍ ሁሉ በተወሰነ ምርት ላይ ቢሰማራ ጥቅም ያገኛል ፤ ኢኮኖሚውንም ሊያሳደግ ይችላል ይለናል። በሌላ አነጋገር ፣ በጊዜው በቴክኖሎጂ መጥቃ የሄደቸው እንግሊዝ በዚህ መስክ ስትገፋና የዓለምን ገበያ በኢንዱስትሪ ምርት ስታጥለቀልቅ ፣ ሌሎች አገሮች ግን ጥሬ ሀብትንና የእርሻን ውጤት ለዓለም ገበያ ማቅረብ አለባቸው። በዚህ መሰረት የሰው አስተሳሰብ ተለውጦ ህብረተሰብአዊ ለውጥ መምጣ ሲችል ፣ በአንድ መስክ ላይ የሚሰለጥኑት አገሮች ዋጋን በመቆጠብና ወደ ሚሰለጥኑበት መስክ በማሸጋሸግ የበለጠ ስለሚያመርቱ አጠቃላይ ህብረተሰብአዊ ጥቅም ማግኘት ይችላሉ ይለናል። በብዛት ያመረቱትን የእርሻም ሆነ ሌላ የተፈጥሮ ሀብት ካለምንም ችግር የዓለም ገበያ ላይ ማራገፍና ለዕድገት የሚሆናቸውን የውጭ ከረንሲ ማግኘት ይችላሉ። እነ አዳም ስሚዝ እንደዚህ ዐይነቱን ቲዎሪ በዘመኑ ሲያስፋፉ ብዙ አገሮች ተመሳሳይ ምርት እንደሚያመርቱና እየጠበበ በሚመጣው የዓለም ገበያ ላይ ማራገፍ እንደማይችሉ አስቀድመው ሊያዩ አልቻሉም። ይሁንና አዳም ስሚዝም ሆነ ሪካርዶ በጊዜው እያደገ የመጣውን አዲሱን የእንግሊዝ ካፒታሊስት መደብ ጥቅም አስጠባቂዎች ለመሆናቸው በጊዜው የነበረውን ውይይትና ጽሁፎቻቸውን ላገላበጠ ወዲያውኑ ሊረዳ ይችላል። በ17ኛው ክፍለ ዘመን ብቅ ያለው ላይብኒዝ የሚባለው ጀርመናዊው ሳይንቲስት ይህ የእንግሊዝ ፍልስፍና ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነትን ካገኘ ለጦርነት ምንጭ ሊሆን ይችላል ብሎ ሲያረጋግጥ ፣ በአስራ ስምንተኛውና በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን ብቅ ያሉት የፖለቲካ ኢኮኖሚ ምሁራን ደግሞ በእነ አዳም ስሚዝ ኢኮኖሚ ቲዎሪ መሰረት አገሮች ዕውነተኛ ዕድገትን ማምጣት አለመቻላቸው ብቻ ሳይሆን ፣ እንደ ህብረተሰብ ለመኖር የማይችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል በማለት ያልተቆጠበ ትግል አደረጉ። ብዙ የሶስተኛው

ዓለም አገሮች በእንደዚህ ዐይነቱ የስራ ክፍፍል ውስጥ መካተት ከጀመሩበት ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የምናየው ሁኔታና ዛሬም በእነዚህ አገሮች አፍጦ አግጦ ያለው ሁኔታ የሚያረጋግጠው ይህ ዐይነቱ ከዕውነተኛው የሰው ልጅ የመፍጠር ችሎታ የራቀ የኢኮኖሚ ፍልስፍና ተግባራዊ እየሆነ በመምጣቱ ነው። ወደ ምዕራብ አውሮፓ ስንመጣ ግን የእንግሊዝን ግፊት ለመቋቋም ሆነ መክቶ ለመመለስ ጀርመንም ሆነ ፈረንሳይ እንደ የሁኔታው ገበያቸውን መከላከል ወይም በመሀከላቸው የነበረውን የከረንሲም ሆነ የንግድ ስምምነት ማፍረስ የተገደዱበት ሁኔታ በታሪክ ተመዝግቦ ይገኛል። ስለሆነም ጀርመንና ፈረንሳይ የግዴታ ወደ ውስጥ ያተኮረ ፖሊሲ ተግባራዊ በማድረግ የውስጥ ገበያቸውን ማሳደግ ችለዋል። በተለይም ጀርመን በአጭር ጊዜ ውስጥ እንግሊዝን መቅደም ቻለች። የጀርመን ፈላስፋዎችና የፖለቲካ ኢኮኖሚ ምሁራን በመጀመሪያ ያተኮሩት በዕውቀት ላይ ነው። ስለዚህም ጀርመን የገጣሚዎችና የደራሲዎች አገር ተብላ ስትታወቅ ፣ በከፍተኛ ደረጃ የፍልስፍና ዕውቀት የዳበረባት ፣ የክላሲካል ሙዚቃ የተደረሰባት አገር ለመሆን በቃች። ይህም የሆነበት ምክንያት አንድ አገር በዕውቀት ካልተካነችና ይህንን መሰረት አድርጋ አጠቃላይና ሰፋ ላለ የስራ ክፍፍል የሚያመች የኢኮኖሚ ፖሊሲ መንደፍ ካልቻለች ዕውነተኛ ሀብረተሰብአዊ ዕድገት ሊመጣ አይችልም የሚለውን መመሪያ አጥብቃ በመያዟ ነው። ዛሬም ቢሆን ሰፊ የኢንዱስትሪ መሰረትና ተስተካክለውና ተደራጅተው የተገነቡ ከተማዎች በአሜሪካንና በእንግሊዝ ሳይሆን ያሉት ፣ በጀርመን ነው የሚገኙት። ያለው ሀቅ ይህ ነው።

ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ አሜሪካ የበላይነቱን ሲቀዳጅ ይህንን አገር አፍራሽ የነጻ ገበያና ንግድ ፍልስፍና ነው ማስፋፋት የጀመረው። በተለይ ከ1950ዎቹ ጀምሮ በከፍተኛ ደረጃ የነጻ ንግድ መሰረት የሆነው የኒዎ-ሊበራል ርዕዮተ-ዓለም መስፋፋትና ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት እያገኘ የመጣው አሜሪካን በኢኮኖሚ ብቻ ሳይሆን በፖለቲካና በሚሊታሪም ብቸኛው ኃያል መንግስት ሆኖ ብቅ ማለት ከጀመረ ወዲህ ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ እንደ ዓለም ባንክ ፣ የዓለም ገንዘብ ድርጅት ፣ በኋላ ደግሞ አሁን ስሙን ለውጦ የዓለም ንግድ ድርጅት(WTO) ተብሎ የሚጠራው የተመሰረቱትና ብዙ ሊትሬቸሮችና የየአገሮች ኢኮኖሚ አወቃቀርም እንደሚያረጋግጠው ከአሜሪካን ጥቅም አንጻር ነው። የውስጣቸው አወቃቀር ፣ የኮታ ጉዳይንና ፍልስፍናውን ለተመለከተ ድርጅቶቹ ባለፈው ስድሳ ዐመታት የተከተሉት ፖሊሲ የአሜሪካንን ጥቅም ያስቀደመ ነው። ይህን አሌ ማለት አይቻልም።

ከዚህ ስንነሳ በተለይም የዓለም ንግድ ድርጅት በድሮው ቅርጹም ሆነ በአዲሱ መልኩ ከታወቀረ በኋላ ብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች አባል ቢሆኑም ፣ በአንድ በኩል ወደ ውጭ የንግድ መጠናቸው ትንሽ ቢጨምርም ፣ በዋጋዎች ከፍና ዝቅ ማለት አስተማማኝ የውጭ ከረንሲ ሊያገኙ አልቻሉም ፤ በሌላ ወገን ደግሞ ወደ ውስጥ በዕውነተኛ የስራ ክፍፍል ላይ የተመሰረተና የየሀብረተሰቡን የማሰብ ኃይል ከፍ ሊያደርግ የሚችል የኢኮኖሚ ዕድገት ተግባራዊ ሊያደርጉ በፍጹም አልቻሉም። ብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች አይ በዚያው ባሉበት እንዲቀሩ ተገደዋል ፤ ወይም ደግሞ በተከተሉትና በሚከተሉት የተበላሻ በነጻ ገበያ ላይ በተመሰረተ ፖሊሲ የተነሳ ሌላ ዕዳና ዝብርቅርቅ ሁኔታ ውስጥ በመግባት ህዝቦቻቸው በስነ-ልቦናና በማቴሪያል እንዲራቆጡ ተገደዋል። ሊወጡት የማይችሉት የተወሳሰበ ችግር ተፈጥሯል ማለት ነው!!

## ግልጽ ያልሆነና ኢ-ዲሞክራሲያዊ አወቃቀር !

የዓለም ንግድ ድርጅት ከአንድ አገር ወይም ደግሞ ከጥቂት አገሮች ጥቅም አንጻር የተቋቋመ እንደመሆኑ መጠን 1ኛ) ላይ እንደተዘረዘረው ድርጅቱ የሚመራበት ፍልስፍና ፀረ-ሳይንስና ፀረ-ስልጣኔ ነው ፤ 2ኛ)አወቃቀሩም ሆነ አሰራሩ ፀረ-ዲሞክራሲያዊ ነው። የመጀመሪው አንድን ቲዎሪንና የአሰራር ዘዴን ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት እንዲኖረው በማድረግ የተለያዩ ችግሮችንና መነሻቸው ልዩ የሆነውን በአንድ ዐይነትና ተመሳሳይ መንገድ ሊፈታ ይቃጣል። እንደሚታወቀው አንድ የዓለምን ህዝብ የሚያስማማ ጉዳይ አለ። ይኸውም ማንኛውም ህዝብ ሆነ ህብረተሰብ የግዴታ ማምረት ፣ልውውጥና ክፍፍል ( production,exchange and distribution) ማድረግ አለበት። 2ኛ) የሰዎች ፍላጎት እንዲሟላ ከተፈለገ በአንድ አገር ውስጥ የግዴታ የስራ ክፍፍል መዳበር አለበት። ይህ ሁኔታ የግዴታ ወደ ገበያ ኢኮኖሚ ያመራናል ማለት ነው። ወደ

ንጹህ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ ስርዓት ያምራ አያምራ በብዙ ነገሮች ነው ሊወሰን የሚችለው። እስከዚህ ድረስ መስማማት ካለ ፣ በሌላ ወገን ግን አሜሪካን አገር የሰፈነው ወይም ደግሞ እንግሊዝ የተጓዘችበትን መንገድ ለሌላውም ማገልገል ይችላል የሚል የተፈጥሮ ህግ የለም። አንዳንድ ትምህርቶችን ግን መቅሰም ይቻላል። ይሁንና እንደ ፊዚክስ ፣ ኬሚስትሪና ባይሎጂ የመሳሰሉት ዓለም አቀፋዊ ባህርይ ቢኖራቸውም ፣ ኢኮኖሚክስ የተፈጥሮ ሳይንስ እንዳለመሆኑ መጠን ዓለም አቀፋዊ ባህርይ ሊኖረው አይችልም። የየአገሮች ባህል ፣ ታሪክና የአኗኗር ስልቶች እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ መጠበቅ ስላለባቸውና ፣ ራሳቸውም ራሳቸውን ስለሚከላከሉ የሌላን አገር አሰራርና አበላል አምጥቶ አንድ አገር ውስጥ ልትከል ቢሉት የባህል ቀውስ ይፈጥራል። ካለብዙም ውጣ ውረድ ከ1950ዎቹ ጀምሮ በሶስተኛው ዓለም አገሮች በልዩ ልዩ ስም ተግባራዊ የሆኑትን ፣ በመሰረቱ የነጻ ንግድ ፖሊሲዎች ስንመለከት ፣ ጥሩ ውጤት ማምጣት ያልቻሉት የየአገሮችን ባህል ፣ ስነ-ልቦናና የማቴሪያል ሁኔታዎች በሚገባ ለመገምገምም ሆነ ለመረዳት ባለመቻልና ባውቃለሁ ባይነት እንዲቀበሉት በማድረግ ነው። በዚህም ምክንያት የፍጆታ አጠቃቀሞች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም ልማዶች በመወሰዳቸው የአስተሳሰብ መዘበራረቅንና የባህልን መበላሸት ሊያስከትል ችሏል። በአገሮች መሀከል የግዴታ የንግድ ግኑኝነት መኖር ያለበት ቢሆንም ፣ በሌላ ወገን ግን አንድ አገር የዚህ ወይም የዚያኛው ኢኮኖሚያዊም ሆነ የንግድ ድርጅት አባል መሆን አያስፈልጋትም። የለም የግዴታ አባል መሆን አለባት ከተባለ ደግሞ የሚያመጣውን ጥቅምና ጉዳት በሚገባ መገምገም የሚያስፈልግ ይመስለኛል። ይህ ደግሞ ብዙ ልፋትንና ወጪን የሚጠይቅ ብቻ ሳይሆን አገዛዙም ሆነ ኤሊቱ በሆነው ባልሆነው ነገር በመነታኮር ዕውነተኛውን የዕድገት ፈለግ እንዳይዙና ተጨባጭ ስራ እንዳይሰሩ ይታገዳሉ። ይህም ፀሀፊ በዚህ ዐይነቱ ለምንም የማይጠቅምና ሳንሳዊ ይዘት በሌለው ነገር ላይ መረባረብ ባላስፈለገው ነበር።

ዛሬ የዓለም ንግድ ድርጅት ተብሎ እንዲጠራና ተግባሩም ከንግድና ንግድን ከመሳሰሉ ነገሮች አልፎ ዕድገትን ፣ የአካባቢ ቀውስን እንዲሁም ሌሎች ለዕድገት ይጠቅማሉ ብሎ የታሰቡትን ያካተተ ቢሆንም ፣ እንደ ታሰበውና ስምምነት እንደተደረሰበት ብዙ ነገሮች ተግባራዊ መሆን አልቻሉም። እ.አ በ1995 ዓ.ም ድርጅቱ ስሙን ለውጦ የዓለም ንግድ ድርጅት ተብሎ እንዲጠራና በመግቢያውም ላይ ጤናማና ለተስተካከለ ዕድገት(Sustainable development) ጠበቃ ሆናለሁ ቢልም እስካሁን በተግባር እንደታየው የተቃራኒው ነው እየሆነ የመጣው። በሌላ አነጋገር ጤናማ ዕድገትና የአካባቢን እንክብካቤ የሚመለከት ክንውን ተግባራዊ ሲሆን በፍጹም አይታየም። ለዚህ ምክንያቱ ምንድን ነው ?

የንግድ ድርጀቱ ወደ 150 የሚጠጉ አባል አገሮች ቢኖሩትም የድርጅቱን ህልውና የሚወስኑ ሁለት አህጉሮችና ሁለት አገሮች ናቸው። እነዚህም ሰሜን አሜሪካ ፣ የአውሮፓ አንድነት ፣ ጃፓንና ካናዳ ናቸው። ከ70% በላይ የሚሆነው ንግድም ሆነ የመዋዕለ-ነዋይ እንቅስቃሴ(FDI= Foreign direct investment) በእነዚህ አገሮች መሀከል የሚካሄድ ነው። እነዚህ አገሮች ከብዙ መቶ ዐመታት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የአሰራር ስልትና ህግን ስለዳበሩ በቀላሉ ሌሎች ደካማ አገሮችን ሊያታልሉበት የሚችሉባቸው መሳሪያዎች አላቸው ማለት ነው። በዚህም ምክንያት እነዚህ ሁለት አህጉሮችና ሁለት አገሮች አንድ ድርጅቱን የሚመለከት ስብሰባ ከመደረጉ በፊት ርስ በራሳቸው በመገናኘት ስምምነት ላይ ይደርሳሉ። በዚህም ምክንያት ይህንን የደረሱበትን ስምምነት በሁሉ አባል አገሮች ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው የተወሰኑ አገሮችን በቡድን ቡድን እየመረጡ ያነጋግራሉ። በዚህ መልክ አንድ ውሳኔ ላይ ከመደረሱ በፊት በትናንሽ አገሮች ላይ ግፊት ያደርጋሉ። የሶስተኛው ዓለም አገሮች በድርጅቱ ውስጥ በቁጥር ከፍተኛውን ቦታ ቢይዙም ዋና ወሳኞቹ እነዚህ ጥቂት የኢንዱስትሪ አገሮች ናቸው።

ይህ ሁኔታ የመነጨው ራሱ ድርጅቱ ባለው ውስጣዊ ፀረ-ዲሞክራሲያዊ አወቃቀር ነው። አብዛኛውን ጊዜ ወሳኞቹ የሚኒስተሮች ጉባዬ ሲሆን ፣ በተለይም ደግሞ በህገ-ደንቡ ላይ ያልሰፈረ የዝቅተኛ ሚኒሰተሮች ጉባኤና በደርጅቱ የተመረጡ አገሮች ጥቂት ተጠሪዎች የሚወስኑት የመነጋገሪያና መጨረሻም የመስማሚያ ነጥብ ይሆናል ማለት ነው። ይህን አሰራር አስመልክቶ የአሁኑ የድርጅቱ ዋና ጸሀፊ ሚስተር ላሚ በ1999ና 2003 ዓ.ም በሰጡት ማብራሪያ የንግድ ድርጀቱ የማዕከለኛውን ዘመን የመሰለ ወደ ኋላ የቀረ አዋቃቀርና አሰራር እንዳለው በግልጽ ተናግረዋል። ስለሆነም የዜና ማሰራጫ ወኪሎችም ሆኑ የሲቪሉ ማህበረሰብ የዓለም ንግድ ድርጅቱ የቀን ተቀን በሚያካሂደው ስራና የሚኒስተሮች ስብሰባ ላይ ተገኝተው ሁኔታውን የማዳመጥና

የመገምገም መብት የላቸውም። ይህም ማለት ውይይቱና ለአጀንዳ የሚቀርቡት ነጥቦች በተዘጋ ችሎት የሚወሰኑ ናቸው ማለት ነው። ግልጽነት የሌለው አሰራር ነው ማለት ነው።

ከዚህ ስንነሳ የንግድ ድርጅቱን ስምምነትና ህግ የሚጥሱ አገሮች የሚቀጡት በእነዚህ ጥቂት ኢንዱስትሪ አገሮች ቀድሞውኑ በተደነገገ ህግ መሰረት ነው። ዳኛውም ከሳሹም አንድ ናቸው። በዚህም ምክንያት አንዳንድ አገሮች የድርጅቱን የንግድ ስምምነት ሲጥሱ ፣ ወይም ደግሞ በሁለት አገሮች መሀከል ከንግድ ጋር የተያያዘ ጠብ ሲፈጠር ደርጅቱ በሚያዘጋጀው አስታረቂ ኮሚት ጥብቅ በሆነ የአሰራር ዘዴ መፈታት አለበት። ውሳኔ የተጣለበት አገር በጥብቅ የዳኞችን ቅጣት በተግባር ማዋል አለበት ማለት ነው። እንደዚህ ዐይነቱን ቅጣት የኢንድስትሪ አገሮች መቋቋም ቢችሉም የሶስተኛው ዓለም አገሮች ግን ሊቋቋሙት በፍጹም አይችሉም። አብዛኛውን ጊዜ እንደዚህ ዐይነቱ ፍርድና ውሳኔ የኢንዱስትሪ አገሮችን የሚጠቅም ነው ማለት ነው።

እስካሁን ድረስ ያለው ልምድ እንደሚያረጋግጠው የንግድ ውይይቱ በተራ ነጋዴዎች መሀከል የሚደረግ ዐይነት ነው የሚመስለው። ይህንን ከሰጠኸኝ ያንን እሰጥሀለሁ የሚመስል ዐይነት ውይይት። አብዛኛውን የንግድ ስምምነቶች የተካሄዱት እ.አ በ1986-1994 የኡራጋይ ዙሪያ ተብሎ በሚታወቀው ሲሆን ፣ ከዚያ በኋላ የተደረጉትና የሚደረጉት ውይይቶችና የተደረሰባቸው ስምምነቶች ይህንን መሰረት ያደረጉ ናቸው። ሁሉም አባል አገሮች ስምምነቶቹን በግዴታ ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው። በየንግድ ድርድሮች ላይ ሌሎች አርእስቶችም በተከታታይ ይካሄዳሉ። ይሁንና የንግድ ስምምነቱም ሆነ ሌሎችም ነጥቦች በአንድ ቀን ይደመደማሉ። እንደዚህ ዐይነቱ ውይይትና የተለያዩ ነጥቦችን አንስቶ ወደ ስምምነት ለመድረስ መጣደፍ ልምድ የሌላቸውን አገሮች መጉዳቱ ብቻ ሳይሆን ደካማ አገሮች ጥቂት ጥቅም አገኘን ብለው ሊወጡ የማይችሉት ስምምነት ውስጥ እንዲገቡ ይገደዳሉ ማለት።

በንግድ ድርጅቱ ህግና ስምምነት መሰረት የአመራረት ፣ የአጠቃቀምና በአጠቃላይ ደግሞ የአካባቢን እንክብካቢ የሚመለከቱ ጉዳዮች ይጣሳሉ። የየአባል አገሮች የስራ ሁኔታና የአከፋፈል ጉዳይ በድርጅቱ ደንብ ውስጥ የተካተቱ አይደሉም። ዋናው ነገር ምርትን አምርቶ በዓለም ገበያ ላይ ማራገፍ ነው።

ለምሳሌ የሚመረቱት ምርቶችና በዓለም አቀፍ ደረጃ ላይ የሚራገፉት ከንጹህ ነጻ ንግድ አንጻር እንጂ ለሰው ጤንንት ይስማሙ አይስማሙ ፣ በምርቶች ውስጥ ያሉት ጤንነትን የሚያቃውሱ ኬሚካሎችና አካባቢን የሚመርዙ ማዳበሪያና የተባይ ማጥፊያ በድርጀቱ እስከዚህም ክትትል የሚረግባቸው አይደሉም። በድርጅቱ አባሎች መሀከል የሚደረጉት የምርት ልውውጦች በእኩልነት የሚታዩ ናቸው። በሌላ አነጋገር ማንኛውም ምርት በዝቅተኛ ደረጃ መታየት የለበትም። ለምሳሌ አንድ አገር የድርጅቱ አባል ከሆነች የአውሮፓ ወይም የአሜሪካ ስጋ ለህዝቤ ጤንነት ሊስማማ አይችልም ብላ እምቢ ልትል አትችልም። በዚህም ምክንያት ለአገሯ ህዝብ የማይጠቅምንና ጤንነትን የሚያቃውሱ ምርቶች በእኩልነት(non-discriminatory) መታየት አለባቸው በሚል የማያስፈልጋትን ምርት ወደ አገሯ እንድታስገባ ትገደዳለች። አንድ አገር ለህዝቧ በቂ ስጋ ወይም እህል ማምረት ብትችልምና የተከማቸ ቢኖራትም አባል ከሆነች የግዴታ ማስገባት አለባት ማለት ነው። በዚህም ምክንያት ለምሳሌ በጥራታቸው ጥሩ የሆኑ የኦርጋኒክ ምርቶች በኬሚካል ማዳበሪያ ከተመረቱት በላይ ሆነው መታየት የለባቸውም። ለምሳሌ በንግድ ድርጅቱ ደንብ መሰረት ኦርጋኒክ ምርቶች ናቸው ፤ ለጤንነት ይስማማሉ ተብሎ በማሸጊያዎች ላይ መጻፍ ወይም ምልክት መደረግ የለበትም። በንግድ ድርጅቱ ህግ መሰረት እንደዚህ ዐይነቱ አሰራር የነጻ ንግድን እንቅስቃሴ ያግዳል። በዚህም ምክንያት የተፈጥሮን ህግና የአካባቢን መጠበቅ የሚያስቀድሙና ለሰው ልጅ ጤንነት የሚስማሙ የአስተራረስና የአመራረት ዘዴዎች በንግድ ድርጅቱ ቦታ አይሰጣቸውም።ምክንያቱም ለየት ያለ አስተራረስና የዘር አጠቃቀም የዓለም አቀፍ ኩባንያዎችን ጥቅም ስለሚጻረር ነው። ሁሉም አባል አገር እንደፈለገው አምርቶ በዓለም ገበያ ላይ ማራገፍ ይችላል ማለት ነው። በዚህ ዐይነት የነጻ ንግድ ስምምነት ላይ የተመሰረተ የአመራረት ዘዴ በአካባቢ ላይ የሚያስከትለውን ቀውስና ቀውሱን ለማስወገድ የሚወጣው ወጪና በመጭው ትውልድ ላይ ሊያስከትል የሚችለውን አደጋ ከግንዛቤ ውስጥ የሚያስገባ አይደለም ማለት ነው። በዚህም ምክንያት የንግድ ድርጅቱ ስምምነትና ደንብ እ.አ በ1992 ዓ.ም በሪዮ በብራዚል የተደረገውን የዓለም ማህብረሰብ ጤናማ የአመራረት ዘዴና የአካባቢን እንክብካቤ መጠበቅ አለበት የሚለውን ደንብ የሚጥስ

ነው። ስለሆነም የኢንዱስትሪ አገሮች በአካባቢ ላይ ጉዳት ለሚያደርሱ ለትላልቅ አራሽ ገበሬዎች ያሚያደርጉትን ድጎማ የንግድ ድርጅቱ ምንም ዐይነት ተቃውሞ አያሳይም። እንደሚታወቀው ማንኛውም የመንግስት ድጎማ የነጻ ገበያን የሚጻረር ሲሆን የንግድ ድርጅቱ ግን እርስ በርሱ የሚቃረን ፖሊሲ ያካሂዳል። በዚህም ምክንያት የነጻ ንግድ ስምምነት ከጤንነትና ከአካባቢ መናጋት በላይ የሚታይ ነው።

በአለፉት አስር ዐመታት የንግድ ድርጅቱ ማድረግ ከሚገባው በላይ ብዙ ነገሮችን በደንቡ ውስጥ እያካተተና ውስብስብ እያደረገ የመጣ ነው። ለምሳሌ የመዋዕለ-ነዋይ(investment) ጉዳይ በንግድ ድርጅቱ ደንብ ውስጥ መካተት እንደሌለበት ተከራካሪዎች አጥብቀው ያነሳሉ። የንግድ ድርጅቱ አባል አገሮች የፓቴንት ስይስተም ማስገባት አለባቸው። ይህ ዐይነቱ የፓቴንት ወይም ፈቃድ አትክልቶችንና ሌሎች ጠቃሚ አፅዋትን ፣ እንስሶችንና የሰውንም ጂን ይመለከታል። በዚህም መሰረት ሳይንስና ቴክኖሎጂ ያላቸው የኢንዱስትሪ አገሮች አንድ ደካማ አባል አገር ሄደው በምርምርም ሆነ በአጋጣሚ አንድ ነገር ካገኙ ይህንን ለራሳቸው ፓቴንት ማድረግ ይችላሉ። ይህም ቀጥተኛ ዘረፋን( Bio piratery) ያስከትላል።

የመጨረሻም በጉልህ እንደሚታው የንግድ ድርጅቱ የምዕራብ አውሮፓና የአሜሪካን እንዲሁም የጃፓንን ትላልቅ ኩባንያዎች ጥቅም የሚያራምድና በነሱ ቁጥጥር ስር የወደቀ ነው። አብዛኛው ውሳኔዎችም በትላልቅ ኩባንያዎችና በድርጅቱ የተዘጋ ችሎች የሚደነገጉና ሌሎች ደካማ አገሮች እንዲቀበሉት የሚደረግ ነው። ስለዚህም እንደ ኢትዮጵያ የመሰለች ደካማ አገር የእነዚህ ኩባንያዎች መጨፈሪያ ከመሆን በስተቀር ለዕድገቷ የሚሆን ጥቅም በፍጹም ልታገኝ አትችልም። ይህንን በሚገባ ለመረዳት አገራችን አባል ብትሆን ሊደርሳባት የሚችሉትን ጠንቆች ዘርዘር እያደረግን እንመልከት።

## <u>በኢኮኖሚው ላይ የሚኖረው ተጽዕኖ !</u>

አንድ አገር እንደዚህ ዐይነት የንግድ ስምምነት ውስጥ ስትገባ በዚህ አማካይነት ብዙ አምርቼ በአባል አገሮች ገበያ ላይ በማራገፍ ለውስጥ የኢኮኖሚ ዕድገት አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር እችላለሁ ብላ በመገመት ነው። ምርቷን በዓለም ገበያ ላይ ስትሸጥ ፣ የውጭ ካረንሲ በማግኘት 1ኛ) ራሷ ማምረት የማትችለውን የፍጆታ ዕቃ ገዝታ በማስገባት ገዝቶ ለመጠቀም ለሚችለው ገበያ ላይ ለማቅረብ ፣ 2ኛ) የምርት ማምረቻዎችንና ሌሎች የረዥም ዕድሜ ያላቸውን ዕቃዎች በማስገባት ኢኮኖሚውን በማደረጀት የውስጥ ገበያዋን ለማዳበር ነው። ለዚህ ደግሞ በዓለም ገበያ ላይ የምታቀርበው ምርት ወሳኝ ሚናን ይጫወታል። ለምሳሌ ብዙ አባል አገሮች ተመሳሳይ ምርት የሚያመርቱ ከሆነ ገበያው ከሚችለው በላይ ስለሚሆን እንደልቧ ብዙ ምርት አራግፋ በቂ የውጪ ከረንሲ ልታገኝ አትችልም። እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ ወደ ውጭ የምትልካቸው ምርቶች አብዛኛውን ጊዜ የእርሻና ከእርሻ ጋር የተያያዙ የምርት ውጤቶች ናቸው። ምርቶቹ ደግሞ በጥሬ መልክ ስለሚቀርቡ ተሸጠው የሚያስገቡት ገቢ ለዕድገት የሚያመጡት ጥቅም እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ያለፈው ስድሳ ዐመት ልምድ እንደሚያረጋግጠው በተሳሳተ የኢኮኖሚ ፍልስፍናና ፖሊሲ በመመራቷ ፣ በአንድ በኩል ወደ ውጭ የምትልከው የምርት መጠን ሊያድግ አልቻለም ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ወደ ውስጥ ኢኮኖሚው በአዲስ መልክ ተደራጅቶ ለህዝቡ የስራ መስክ በመክፈትና ገቢውም አድጎ ኑሮው እንዲሻሻል አላደረገም። በሚቀጥሉት ጊዜያት አባል የመሆን ዕድል ብታገኝ ይህ ሁኔታ ሊሻሻል ይችላል ብሎ መገመት የዓለምን ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በሚገባ ጠጋ ብሎ ለመመርመር አለመቻልና በነጻ ገበያ ርዕዮተ-ዓለም መታወር ነው።

ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት መሆን አለባት ብሎ የኢህአዴግ አገዛዝም ሆነ አንዳንድ አዲስ መጤ አኮኖሚስቶች ሲወተውቱ በግምት ውስጥ የሚያስቀምጡት ሌላው ምክንያት በዚህ አማካይነት የውጭ ከበርቴዎች መጥተው በአገራችን ኢንቬስት በማድረግ የስራ መስክ ይከፍታሉም ፤ ኢኮኖሚው ሊያድግ ይችላል ከሚል የተሳሳተ አመለካከት በመነሳት ነው። የስድሳ ዐመቱን የዓለም አቀፍ ኩባንያዎች እንቅስቃሴ የተከታተለ ፣ ኩባንያዎቹ አንድ አገር የተሟላ ኢንዱስትሪን ተክለው አያውቁም። አብዛኛውን ጊዜ በሶስተኛው ዓለም አገሮች የሚመረቱ ምርቶች እንደ መለዋወጫ ዕቃዎች ያሉ ናቸው ፤ ወይም ደግሞ የመለዋወጫ ዕቃዎች በተለያዩ አገሮች ከተመረቱ

በኋላ በሌላ አገር ይገጣጠማሉ። እንደምርምርና ዕድገት(Research and Development) የመሳሰሉት በሶስተኛው ዓለም አገሮች ተካሂደው አያውቁም። በተለይ ከ1990ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ በብዙ ዓለም አቀፋዊ ኢንቬስተሮች የተያዘው በቀጥታ ከምርት ጋር የተያያዘ መዋዕለ ነዋይ ሳይሆን ፣ በህንፃ ስራ(real state) ላይ መሰማራትና ሆቴል ቤቶችን ማስፋፋት ነው። ለህንፃ ስራ የሚያገለግሉ አብዛኛዎቹ ማቴሪያሎች ደግሞ ከውጭ የሚመጡ ናቸው። ለምሳሌ አዲስ የንግድ ድርጅቱ አባል የሆነትው ቬትናም ከአገሯና ከህዝቧ ፍላጎት ጋር የሚሄድ ታሪካዊና ለሰፊው ህዝብ ጥቅም የሚያገለግሉ ህንፃዎች ከመስራት ይልቅ የኢንቬስተሮችን ፍላጎት ለማሟላት በሚል ባህሏ እንዲበላሽና ጥገኛ እንድትሆን ተደርጋለች። አንዱ የህብረተሰብ ሳይንስ ምሁር እንዳለው እንደዚህ ዐይነት ህንጻዎች ፀረ-አርኪቴክቸር (anti-architecter) ናቸው። ውበትና ዕድሜ የሌላቸው። መጨረሻ ላይ ተገትሮ የሚታይ ህንጻ ከማየትና ከመዝናናት በስተቀር በውጭ ኢንቬስትሜንት አማካይነት የሚካሄደው እንቅሳቃሴ እዚያው በዚያው የሚሽከረከር ነው ማለት ነው። ኢኮኖሚውን የማሳደግ ኃይል የለውም። ባለፉት 18 ዓመታት በአገራችንም ሲገነባ የነበረው ህንጻ ከህዝቡ ፍላጎት ጋር የተጣጣመና ታሪካዊነት ያለው ሳይሆን የጥቂቶችን ፍላጎት የሚያረካ ብቻ ነው። ብዙ የመብራት ኃይልና ውሃ የሚጋራ። በተጨማሪም አሁን አገራችንና ቬትናምም እንደሚታየው የውጭ

ከበርቴዎች እየመጡ መሬት በመከራየትና ህንጻ በመስራት ተራውን ህዝብ ይጋፋሉ(crowding out) ፤ በዚህም ምክንያት በሀብታምና በደሀ መሀከል ያለው ልዩነት መስፋቱ ብቻ ሳይሆን አገራችን ከህዝቡ ባህልና ታሪክ ጋር እየተነፃፀረ የሚሄድ የቤት አሰራር ተግባራዊ እንዳታደርግ ትታገዳለች። እነ አላሙዲንና አሁን ደግሞ ሰን ሻይን በመባል የሚታወቀው ኢህአዲጎች ከበስተጀርባው ያሉበት የህንጻ ስራ እንቅስቃሴና በራሱ ሰን ሻይን በ10.5 ቢሊዮን የኢትዮጵያ ብር ከውጭ ከበርቴዎች ጋር ሆኖ የሆቴል ቤት ለመስራት የተደረሰበት ስምምነት አደጋው ከላይ የተዘረዘረውን የሚጋብዝ ነው።

በአዲስ አበባም ሆነ በአዋሳ ከተማ የሚሰሩት ሆቴል ቤቶች ከአገሪቱ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የተጣጣሙ አይደለም። ሎጂክንና የአንድን አገር የህብረተሰብ ፍላጎትና የዕድገት ሁኔታ ያላካተተ የህንፃ አሰራር እዚህና እዚያ ካለ ዕቅድ ይሰራል። የሚሰሩት ሆቴል ቤቶች ህብረተሰቡ ከሚጠይቀው በላይ ናቸው። ኢንዱስትሪና የአገልግሎት መስኩ በአገሪቱ በአጠቃላይ የተዘረጋ ከሆነ የግዴታ ለስብሰባም ሆነ ለሌሎች ነገሮች ሆቴል ቤቶችን እንደ ጥያቄው እየታየ ማስፋፋት ይቻላል። ለውጭ ከበርቴዎችና ቱሪስቶች ከሆነ ደግሞ በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች እንደምናየው ከአጭር ጊዜ በኋላ ካለ ጥቅም ተገትረው የሚቀሩ ህንጻዎች ይሆናሉ። ከአየር ላንዳና ከታይላንድ በተማርን ነበርን። በሌላ ወገን ግን ለምን ይህ ሀብት ወደ ሌሎች መስኮች ላይ ሊውል እንደማይችል አይገባኝም። በኛም ሆነ በብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች የተያዘው ፈሊጥ ፣ አንዱ አበባ ሲተክል ሌላውም በዚያው መስክ ላይ ይሰማራል። ሆቴል ቤት ሲሰራ ሁሉም ሆቴል ቤት ሰሪ ይሆናል። አንድ የመኪና መገጣጠሚያ ፋብሪካ ሲቋቋም ሌላውም እንደዚህ ዐይነት ለማቋቋም ይሯሯጣል። የቡና ጥያቄ በዓለም ገበያ ለያ ጠያቂውና ዋጋው ዝቅ እያለ መሄዱ ሲታወቅ በመቶ ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር የቡና ተከላ ይስፋፋል። በተለይም ተማርኩኝየሚለው ለምን እንደዚህ ነገሮችን እያጣመመ እንደሚረዳ በፍጹም ሊገባኝ አይችልም። በአገራችን የሚሰራው ስራ ሁሉ አዲስ ሀብትን የሚፈጥር ሳይሆን ሀብትን የሚያባክንና የህዝቡን የመፍጠር ችሎታ የሚያፍን ነው።

ሁኔታው በዚህ ከቀጠለ መጤ „ከበርቴዎችና“ ከዓለም አቀፍ የፋይናንስ ስርዓት ጋር በጥቅም የተቆላለፉ ወጣት ኢኮኖሚስቶች በሚያደርጉት ያላዋቂዎች ስምምነት ወደ ሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎችም በመሸጋገር ልዩ ዐይነት የህብረተሰብ ኃይል በመፍጠር ለህብረተሰቡ ጠንቅ ይሆናሉ። እንደ ቺሌና አርጀንቲና ሁኔታ ተፈጥሮ ለሪፎርም አስቸጋሪ ሁኔታ ከወደፊቱ ይደቀናል። እነዚህ አዲስ የህብረተሰብ ኃይሎች የራሳቸው ጥቅም የተነካባቸው ስለሚመስላቸው ከውጭ ኃይሎች ጋር በማበር ማንኛውንም ህዝብንና አገርን የሚጠቅም ሃሳብና እርምጃ ሁሉ ይቃወማሉ። በመሆኑም በውጭ ከበርቴዎች የሚደገፍ የእርሻ ምርት እንቅስቃሴ ልክ ላቲን አሜሪካ እንደታየው ወደ ውስጥ አዳዲስ ኦሊጋርኪዎችን በመፍጠርና ሀብትን ወደ አንድ ወገን በማሸጋሸግ ሰፊውን ህዝብ የሚያደኸይና የሚመታ ይሆናል። ከረዥም ጊዜ አንጻር ሜክሲኮና ብራዚል እንደሚታየው የማፍያ እንቅስቃሴ ሊከሰት ይችላል ማለት ነው።

ወደ ባንኩና የቴሌኮሙኒኬሽን መስክ እንምጣ። ኤህአዴግ ስልጣን ከያዘና የነፃ ገበያ ተግባራዊ ማድረግ ከጀመረ ወዲህ ብዙ የግል ባንኮች ተቋቁመዋል። ይህ ግልጽ እየሆነ ለምን የንግድ ድርጀቱ በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉትን ባንኮች የግል ካለደረጋችሁ እያለ እንደሚወተውት ሊገባኝ አይችልም። እንደሚታወቀው በብዙ አገሮች

ከመንግስት ባንኮች ውጭ በግል የሚንቀሳቀሱ ብዙ ባንኮች አሉ። ለምሳሌ የጀርመንን የባንክ አወቃቀር ብንወስድ ሶስት ዐይነት ባንኮች አሉ። ከማዕከላዊ ባንኩ በስተቀር ፣ በዋናው መንግስትና በየፌዴራል ስቴቶች ቁጥጥር ስር ያሉ ለማዕከለኛና ለትናንሽ ኢንዱስትሪዎች እንዲሁም ለቤት ሰሪዎች በርካሽ ብድር የሚሰጡ አሉ። ሁለተኛ ፣ በህብረት ስር የሚተዳደሩና ለአባሎቻቸው ብድር የሚሰጡ። የማህበራዊ ነክ ድርጅቶች ከመንግስት የሚያገኙትን ድጎማ በነዚህ ባንኮች አማካይነት ነው የሚተላለፍላቸው። ሶስተኛ ፣ በግል ስር ያሉ ባንኮች። ከዚህ ውጭ በመንግስት ቁጥጥር ስር ያለ የኢንቬስትሜንት ባንክ አለ። ይህ ዐይነቱ የባንክ ስይስተም ዩኒቨርሳል ባንክ አወቃቀር ይባላል። ባለፉት ስድሳ ዐመታት የጀርመን የባንክ አወቃቀርና አሰራር በዚህ መልክ ሲካሄድ የቆየ ነው። አሁን በደረሰው ዓለም አቀፋዊ የፋይናንስ ቀውስ ብዙ የግል ባንኮች ከመንግስት ድጎማ እያገኙና አንዳንዶች ወደ መንግሰትነት የሚዞሩበት ሁኔታ እየተጠና ነው። ያለው ሀቅ ይህ ከሆነ ለምንድነው የንግድ ድርጅቱ የአቶ መለሰን መንግስት የሚጨቀጭቀው? የገንዘብን ዕድገት ትርጉምንና እንዲሁም ባንክ ለአንድ አገር የኢኮኖሚ ዕድገት ስላለው ሚና በሚመለከት እ.ኢ..አ በ1991 በሚያዚያ ወር በጦብያ መጽሄት ላይ አንድ ጽሁፍ ስላወጣሁ እሱን መመልከቱ አንዳንድ ነገሮችን ግልጽ ሊያደርግ የሚችል ይመስለኛል። ያም ሆነ ይህ የመንግስት ባንኮች ወደ ግል ቢዘዋወሩ ብድር ፈላጊዎች የሚፈልጉትን ብድር በተመጣጣኝ ወለድ ሊያገኙ አይችሉም። ከብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች ልምድ የምንቀምሰው እንዲያውም በባንኮችና በኢንዱስትሪዎች መሀከል ያለው ግኑኝነት ከመላላቱ ባሻገር የገንዘብ መሽከርክር ኃይል ይቀንሳል። አጠቃላይ ህብረተሰብአዊ ሀብት ሊፈጠርና ሊከማች አይችልም።

የስልክንም ጉዳይ ስንመለከት የተሻለ ዕድል ማየት አንችልም። አንዳንድ ቦታዎች ለማመልከት እንደሞከርኩት ባለፉት አስራስምንት ዐመታት በተንቀሳቃሽ ስልክ መስፋፋት የተነሳ ቋሚው ስልክ እየተዳከመ መጥቷል። ወደ ግልሀብትነት ቢሸጋገር የቀረው ቋሚ ስልክ የባሰውን ይዳከማል። ምክንያቱም ኢንቬስተሮች ተንቀሳቃሽ ስልካቸውን ለመሸጥና ትርፍ ለማካበት ሲሉ ወደ ቋሚው ስልክ ላይ ስለማያተኩሩ ነው። የብዙ የሶስተኛው ዓለም አገሮች ልምድ ይህንን ነው የሚያስተምረን።

ያም ሆነ ይህ ከንግድም ሆነ ከአጠቃላይ ኢንቬስትሜንት አንጻር ስንነሳና ሁኔታውን ስንገመግም የእነ አቶ መለስና የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒሰተሩ አካሄድ በምንም ዐይነት ወደ ውስጥ ፣ የውስጥ ገበያ በተስተካከለ መልክ ሊያሳድግና አብዛኛውን ህዝብ ሊያሳትፍ የሚችል የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንዲፈጠር የሚያግዝ አይሆንም። የኢህአዴግ አገዛዝ ስልጣን እስካለ ድረስና ጠቅላላው የኢኮኖሚ ፍልስፍና በነጻ ገበያ ላይ የተመሰረተ እስከሆነ ድረስ ፣ እንዲሁም ኢትዮጵያ የግዴታ የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚው ውስጥ ከመግባት ሌላ ዕድል የላትም የሚለው እንደመመሪያ እስከተወሰደ ድረስ የኢትዮጵያ ህዝቦች በዚህም ሆነ በሌላ አገዛዝ የስልጣኔን ብርሃን ሊጎናጸፉ በፍጹም አይችሉም። አገራችን በሚቀጥሉት ሃምሳና መቶ ዐመታት አዲስ ብቅ እያለ በሚመጣና ንቃተ ህሊናው ዝቅተኛ በሆነ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ኤሊት እያታሸች ለዘለዓለም ታልፋ የምትቀር ትሆናለች ማለት ነው።

## <u>በማህበራዊ ኑሮ ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ!</u>

በመጀመሪያ ደረጃ ግልጽ መሆን ያለባቸው ነገሮች አሉ። በዓለም ንግድ ድርጀቱም ሆነ በሁለቱ እህትማማች ድርጅቶች አንድ አገር እንደ ህብረተሰብ የሚታይ ሳይሆን ፣ ግለሰቦች እዚህና እዚያ በመፘፘጥ ጥቅማቸውን የሚያሳድዱበት መድረክ ነው። ስለሆነም በድርጅቱም ሆነ በሁለቱ ዓለም አቀፋዊ እህትማማች ኢንስቲቱሽኖች ፍልስፍና አንድ ህብረተሰብ ፖለቲካዊ ፣ እሴታዊና ሞራላዊ አይደለም። ታሪክም የሚሰራበት አይደለም። ይህ አመለካከት የድርጅቶቹ ብቻ ሳይሆን የእንግሊዝና የአሜሪካንም ነው። በተለይ ባለፉት ሰላሳ ዐመታት ይህ ዐይነቱ አስተሳሰብ ነው ሲሰበክ የከረመውና ብዙ አገሮችን ያተራመሰው።

ሰለ አንድ ህብረተሰብ የማህበራዊ ሁኔታ ስናወራ ብዙ ነገሮችን መመልከት አለብን። በቤተሰብ መሀከል ያለው የርስ በርስ ግኑኝነት ፣ በልጆችና በወላጆች መሀከል ፣ ልጆች ከተወለዱና የህፃናት መዋያ ዕድል ማግኘት ከጀመሩ ጀምሮ በመንግስት በኩል የሚደረግላቸው እንክብካቤ ፣ የወጣቶች የወደፊት ዕድልና ከመጥፎ ነገሮች እንዲቆጠቡ በመንግሰት በኩል መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች ፣ በሙያ ሰልጥነው ወይም

ትምህርታቸውን ከፈጸሙ በኋላ የሚያጋጥማቸው የስራ ዕድል ፣ የጠቅላላው ህዝብ የአመጋገብ ሁኔታና የማሰብ ኃይል ፣ እንዲሁም የተወሰነው ህብረተሰብ ክፍል ጡረታ ከወጣ በኋላ ሊደረግለት የሚገባው እንክብካቤና በጠቅላላው ህዝብ መሀከል ያለው የርስ በርስ ግኑኝነት የሚጠነክርበት ጉዳይ እንደ ማህበራዊ ጉዳዮች ሊታዩ የሚገባቸው ናቸው። የትምህርትና የጤንነት እንዲሁም ልዩ ልዩ ማህበራዊ ነክ ነገሮች ልዩ አትኩሮ ማግኘት አንድ ህብረተሰብ ተረጋግቶ እንዲኖር ይረዱታል። ከታሪክ አንጻር ሰፋ ያለ የምሁራዊ እንቅስቃሴ የማይታይባቸውና በስልጣን ላይ ያለው አገዛዝ ህብረተሰብአዊ ኃላፊነት የማይሰማው ከሆነ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገሮች ህዝቦቻቸው የማህበራዊ እንክብካቤ ዕድል ሊያገኙ በፍጹም አይችሉም።

ያለፈውን የአስራ ስምንት ዓመቱን የነፃ ገበያንና የመዋቅር ፖሊሲን ስንመለከት በህብረተሰባችን ውስጥ ከፍተኛ የባህል ፣ የማህበራዊና የጤንነት ቀውስ እንዲከሰት አድርጓል። መንግስትም ሆነ ህብረተሰቡ ሊወጡ የማይችሉት ማጥ ውስጥ ገብተዋል። ይህንን ክስተት ከኢኮኖሚው ፖሊሲና ከንቃተ ህሊናው ዕድገት ማነስ ጋር አለማያያዝ ትልቅ ስህተት ነው።

ከላይ በዝርዝር እንደ ሰፈረው ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ብትሆን የህብረተሰቡን ማህበራዊ ኑሮ የሚያናጉ ፣ ጤንነቱን የሚያቃውሱ ፣ ባህሉን የባሰ የሚከሰክሱ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እንድትከትል ትገደዳለች ማለት ነው። በቬትናምና በብዙ የደርጅቱ አባል በሆኑ አገሮች የሚታየው ሁኔታ አብዛኛው ህዝብ በኑሮው ሲሻሻልና እፎይ ብሎ ተዝናንቶ ሊኖር ያልቻለበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው። አዲስ በተፈጠረው የውስጥ ዱርዬ መሳይ ከበርቴና የውጭ ከበርቴ መሀከል በሚፈጠር የኢኮኖሚና የንግድ ግኑኝነት ህጻናትና ወጣት ሰለባ ይሆናሉ። ዘለዓለሙን ጠንቅ የሚሆናቸውን ነገር ተሸክመው ሲሰቃዩ እንዲኖሩ ይገዳደሉ። የድረግ መስፋፋት ፣ የህጻናት መሸጥና ኦርጋናቸውን መሰረቅ ፣ ለአቅመ-አዳም ያልደረሱ ሴት ልጆችን ወደ ብልግና እንዲሰማሩ ማስገደድ ፣ ወጣቱን ማባለግና በአገርና በታሪክ ያልተለመደ ስራ እንዲሰራ ማድረግ ፣ እነዚህ ሁሉ በአይምኤፍ ፣ በዓለም ባንክና በዓለም የንግድ ድርጅቱ የሚሰበኩ የነጻ ገበያ ክስተቶች ናቸው። ያለፈውን የአስራ ስምንት ዓመት የኢኮኖሚ ፖሊሲ ስንመለከት ይህ ሁኔታ ነው ሊከሰትና የህብረተሰቡን ጭንቅላት ሊያዞረው የበቃው።

አዳዲስ ኤንቬስተሮች ቢመጡ በእንቅስቃሴው ውስንነት የተነሳና ከብዙ አገሮችም ልምድ እንደሚታየው የመንግስቱ የቀረጥ መሰረት(Tax Base) ሊሰፋ አይችልም። ኢኮኖሚያዊ መሰረቱ ደካማ የሆነ ህብረተሰብና የታክስ መሰረቱን ሊያሳድግ የማይችል መንግስት ደግሞ በዚህ መልክ ሊከሰቱ የሚችሉ ማህበራዊና ባህላዊ ቀውሶችን ሊቋቋም አይችልም። በአዲሱ የኢኮኖሚ አሌትና በመንግስት መሀከል በሚፈጠረው የጠበቀ ግኑኝነት በአንድ በኩል ፣ በሌላ ወገን ደግሞ ልቅ በሆነው የሰፊው ህዝብ ማህበራዊ ኑሮ ልዩነቱ እየሰፋ ስለሚሄድ በመንግስትና በሰፊው ህዝብ ዘንድ ዘለዓለማዊ አለመተማመንና መፋጠጥ ይኖራል። ይህ ዐይነቱ ከአማሪካንና ከእንግሊዝ የተወሰደ ሰፊውን ህዝብ የሚረግጥ ሞዴል በነዚህ አገሮችም ከፍተኛ ህብረተብአዊ ቀውስ አስከትሏል። እንደዚህ ዐይነቱን ህዝቦችን የመናቅ መንፈስ ደግሞ እንደኛ ባለው ደካማ ኤሊት ጭንቅላት ውስጥ ሲቀረጽ በህዝቡ መሀከል ከፍተኛ መሻከር እንዲፈጠር ይደረጋል። ይህንን ሁኔታ ነው እንግዲህ ከእነ አይ ኤም ኤፍና የዓለም ባንክ ቀጥሎ የዓለም ንግድ ድርጁቱ በግዴታ የሚያስፋፋው። ስለሆነም አገራችን የዚህ ድርጀት አባል መሆን በመቶ ዐመት ውስጥ ልተወጣ የማትችለው ማጥ ውስጥ ይከታትል።

## በአካባቢ ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ!

የአስራ ስምንት ዐመቱ የመዋቅር ፖሊሲና የነጻ ገበያ ሂደት በአገራችን ውስጥ ከፍተኛ የኢኮሎጂ ቀውስ አስከትሏል። በመጀመሪያ መንግስቱና ካድሬዎቹ የውጭ ካረንሲ እንቃርማለን በማለት ያስፋፉትና እንዲስፋፋ ያደረጉት የአበባ ተከላ ከፍተኛ የአካባቢና የጤንነት ቀውስ አስከትሏል። ካለምንም የአፈር ጥናትና ምርምር በመሬቱ ላይ የሚነሰነው ማዳበሪያና የተባይ ማጥፊያ የመሬቱን ምርታማነት መቀነሱ ብቻ ሳይሆን ብዙ በአካባቢው የሚገኙ አጽዋዕትንም እንዲወድሙ አድርጓል። ከዚህ ባሻገር ወደ አስር ሺህ የሚጠጉ ሰራተኞች ለጤንነት ቀውስ ተጋልጠዋል። ብዙ ወጣት ሴቶች የማህጸን ካንሰር እንዳጋጠማቸው ይነገራል። አገራችን በአጭር ጊዜ ውስጥ በዚህ አገዛዝ እንደዚህ ዐይነት የኢኮሎጂ ቀውስ እንዲደርስባት መዳረጓ ታሪካዊ ኃላፊነቱን ያልተገነዘበ መሆኑን

ያመለክታል። ይህ አገዛዝና ካድሬዎች ተው እየተባሉ ከውጭ ኃይሎች ጋር በማበር በበላይነት ያካሄዱት የማን አለብኝነት ስራ አገራችንን መቀመቅ ውስጥ ከቷታል።

በዚህ መልክ ለእርሻ ሰብል የሚያገለግሉ ዘሮችም በጂን እንዲዳቀሉ ሆነዋል። ከሆላንድ በመጣ የቲማቲም ዘር የአገራችን የቲማቲም የተፈጥሮ ዘር እንዲወድም ተደርጓል። በቆሎና አሁን ደግሞ ጤፉችንም ይህ ዕድል አጋጥሟቸዋል። ከዚህ ጋር ተያይዘው ለመኪና ዲዝል የሚያገልግል ዛፍ መተከሉና በአካባቢው ያለው ዛፍ እንዲወድም ማድረግ ፣ ለአውሮፓ የክረምት ገበያ የስትሮው ቬሪ እርሻ እንዲስፋፋ ማድረግና ለሌላ ሰብል ሊያገለግል የሚችለውን መሬት መጋራት ከፍተኛ ቀውስ አስከትሏል። ኢትዮጵያ የዓለም ንግድ ድርጅት አባል ብትሆን የውጭ ምንዛሪ ለመቃረም ሲባል የግዴታ ኢኮሎጂውን በሚቀናቀኑና የህዝቡን ጤንነት በሚያቃውሱ የእርሻ ሰብሎች እንድተሰማራ ትገደዳለች። ያልታቀደ የኢኮሎጂ ቀውስ አገሪቱን ያጋጥማታል ማለት ነው። ምናልባት ወደ ፊት በሚካሄድ ሰፋፊ እርሻና የውጭ ኢንቬስተሮች ተሳትፎ በጠቅላላው የእርሻው ባህል እንዲናጋና ፣ በተለይም ደግሞ የመሬት ውሃ እንዲመረዝ ይደረጋል ማለት ነው።

ይህ ብቻ አይደለም። ባለፉት አስራስምንት ዐመታት በነጻ ገበያው ምክንያት የተነሳና የአገሪቱ ገበያ ልቅ በመሆኑ አካባቢውን የሚያቃውሱ ፣ ብዙ ጪስ ቡልል እያደረጉ ያሚያወጡ ያረጁ መኪናዎች በመግባት አየሩን በርዘዋል። ብዙ ሰው ለአስም በሽታ እንዲዳረግ ምክንያት ሆነዋል። ከዚህም በላይ ብዙም ሳይመረመሩ የሚገቡ የዕቃና የመታጠቢያ ቤቶች ማጽጂያ ኬሚካሎች ወደ መሬት ውስጥ በመግባት ውሃን ሊመርዙ እንደሚችሉ ይታወቃል። ስለሆነም አገራችን የንግድ ድርጅቱ አባል በምትሆንበት ጊዜ በህጉ መሰረት ገበያዋን ክፍት ማድረግ አለባት። በምግብም ሆነ በኢኮሎጂ ላይ የተወሰነ ግደባ ወይም ስታንደርድ ልታደርግ አትችልም። የሚጠቅመውንም የማይጠቅመውንም ወደ አገር በማስገባት የአካበቢን መናጋትንና የጤንነትን መቃወስን ትጋብዛለች። በንግድ ድርጅቱ አዲስ ተጨማሪ ደንብ መሰረት ፣ ድርጅቱ በነጻ አገሮች የአመጋገብና አተካከል ላይ ገብቶ የመደንገግ መብት አለው። ጤናማ ዕድገት የሚለው በደንቡ ውስጥ ቢካተትም ፣ የዘር ዐይነቶችና አስተራረስን በሚመለከት ከኢኮሎጂ አንጻር እየታየ የሰፈረ አንዳችም ነገር የለም ማለት ነው። ስለዚህም ቀደም ብሎ ከቀንድ ከብት ጋር የተያያዘው በሽታና(BSE) የወፍ በሽታ ልክ ዛሬ እንደምናየው የፋይናንስ ወረርሽኝ አገራችንም ውስጥ በመስፋፋት ብዙ ህዝብና አካባቢ አደጋ ውስጥ ሊወድቁ ይችላሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚከሰቱት አንዳንድ ቀውሶች መዳን ባይቻልም ፣ አንድ አገር ገበያዋን ልቅ ካደረገችና ማንም እየመጣ የሚጨፍርባት ከሆነ ፣ በተለይም ደግሞ ለትርፍ ብቻ ተብሎ የኢኮሎጂ ነገር ደንታ አይሰጠንም የሚባል ከሆነ ህዝባዊ እልቂት እንዲደርስ ይደረጋል ማለት ነው።

ሰሞኑን አረንጓዴው ህይቅ የሚለውን አልጃዚራ ያነሳውን ዶኩሜንተሪ ፊልም የተመለከተ በአካባቢና በሰው ልጅ ህይወት ላይ የቱን ያህል ወንጀል እንደሚሰራ ነው። ከአሰሪው ፈረንጅም ሆነ ከባለስልጣኖቹ የሚሰጠው አስተያየት እብሪተኛ ፣ እኛ ስለ አካባቢ አያገባንም ፤ ዋናው የሚታየን ነገር መዝረፍ ብቻ ነው የሚል ነው። በአዲስ አበባ ከተማም ካለምንም ዕቅድና የውሃ ቧንቧ በደንብ ሳይዘረጋና የቆሻሻ ቦይም ሆነ መጣያ ዝግጅት ሳይኖር እዚህና እዚያ የሚሰሩት ህንፃዎች ህዝብ ማጎሪያዎች(Ghetto) ከመሆን አልፈው ወደ ፊት አደገኛ ሁኔታ የሚፈጠርባቸው ቦታዎች ይሆናሉ ማለት ነው። የህንፃ ስራዎቹ ወደ ፊት የሚፈጠረውን አዳዲስ ሁኔታዎች ያላከተቱ ብቻ ሳይሆን ፣ ሌሎችንም እንደ መዝናኛና ኪንደር ጋርተን ፣ እንዲሁም ለእግረኛና ለብስኪሌት መንጃ ተብለው የተዘጋጁ አይመስልም። ለአካባቢው ውበት የሚሰጡና መጠለያ የሚሆኑ ዛፎች ከመጀመሪያውኑ ከቤት አሰራሮች ጋር የታቀዱ አይመስልም። ይህንን የመሰለውን የግብር ውጣ ስራ በኋላ ለማስተካከል በጣም አስቸጋሪ ይመስለኛል።

## <u>ማጠቃለያ</u>

ላይ ከሞላ ጎደል በሰፊው እንደተዘረዘረውና የብዙ አገሮችም ልምድ እንደሚያስተምረን የነጻ ገበያና ንግድ ወይም ደግሞ የእንደዚህ ዐይነቱ ድርጅት አባል መሆን ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን ማምጣት አይችልም። ከፋይናንስ ገበያው ቀጥሎ የተከሰተውና እየጠለቀ የሄደው የተጨባጭ ኢኮኖሚ ቀውስ ብዙ የኢንዱስትሪ አገሮችን አላፈናፍን ብሏል። በአለፈው አንድ ዐመት ተግባራዊ የሆኑት ልቅ የገንዘብ ፖሊሲና

ባንኮች የማዳን እርምጃ የገበያውን ሁኔታ ረገብ ሊያደርገው አልቻለም። በፋይናንስ ላይ ብቻ የደረሰው ቀውስና ወደ ተጨባጩ ኢኮኖሚ እየተዛመተ የመጣው መዛባት ራሳቸውንም መንግስታትንና የኒዎ-ሊበራል ኢኮኖሚ አራማጅዎችንም የስርዓቱን ዘላቂነት እንዲጠይቁ አስገድዷቸዋል። ይህ ሁኔታ እየሰፋና ስር እየሰደደ ሲሄድ የአክስዮን ገበያውም ሆነ ዋጋና በዓለም ላይ የሚሽከረከረው ዕቃ እየቀነሰ መጥቷል። ቻይናና ጃፓን የንግድ ሚዛናቸው ወደ መናጋት ደርሷል። የዘይት አምራች አገሮችም ገቢያቸው በከፍተኛ ደረጃ በመቀነሱ የጀመሩትን ፕሮጀክቶች ሊገፉባቸው አልቻሉም። አሁን እየተፈራ የመጣው ብዙ የኢንዱትሪ አገሮች በሚያደርጉት የውስጥ ድጎማና ኢንዱስትሪዎችንና ባንኮችን የማዳን ፖሊሲ ወደ ዕገዳ(protectionism) ሊያመሩ ይችላሉ የሚል ነው። ከዚህ ጋር ተያይዞ የአውሮፓው አንድነት ገበያ ሊናጋ ይችላል ፤ አይሮን ተግባራዊ ያደረጉ አገሮች ወደ ጥንቱ ብሄራዊ ገንዘባቸው ሊመለሱ ይችላሉ የሚል ፍርሃት አለ። የዓለም ገበያና የካፒታሊዝም ሁኔታ አስተማማኝ አይደሉም ማለት ነው። በእርግጥም ካፒታሊዝም በአለፉት ስድሳ ዐመታት ፣ በተለይም ደግሞ ባለፉት ሃያ ዐመታት የተጓዘበትን መንገድ ይዞ ሊሄድ አይችልም። በዚህ ዐይነት ሀብት ጨራሽነቱና አካባቢን ማቃወስ ሊገፋ እንደማይችል ብዙ ጥናቶች ያረጋግጥሉ። ተፈጥሮና የሰው ልጅ የካፒታሊዝምን ልቅ ሂደት እየተቋቋሙት ነው። ያለው ሀቅ ይህ ነው። በዚህም ምክንያት በፕሬዚደንት ሳርኮሲን ካፒታሊዝምን በአዲስ መልክ ማዘጋጀት የሚለው እንቅስቃሴና የፋይናንስ ገበያውን ለመቆጣጠር የሚያስችል ህግ ለማውጥ ማምራት ካፒታሊዝምና የዓለም ገበያ በድሮ መልካቸው ሊቀጥሉ እንደማይችሉ በመገንዘብ ነው። የጀርመኗ ካንስለርም ሚስስ መርክል ከሁለቱ እህትማማች ድርጅቶች ባሻገር በዩናትድ ኔሽንሸ ቁጥጥር ስር የሚሆን አዲስ የሀብትን አጠቃቀም ዘዴ የሚቆጣጠር ንዑስ ድርጅት መቋቋም አለበት ሲሉ የፊዚክስ ምሁር እንደመሆናቸው መጠን የተፈጥሮን ህግጋት በመረዳታቸው ነው። ከዚህ በተረፈ የቀውሱ ጥልቀት ብዙ ፋብሪካዎች ስራቸውን እንዲያቀዘቅዙና ለጊዜውም ቢሆን ማቆም በመገደዳቸው በብዙ ሺህ የሚቆጠር ሰራተኛ ከስራው እየተባረረ ነው። ቻይና ብቻ 20 ሚሊዮን የሚጠጋ ህዝብ ከስራው ተባሯል። የኢኮኖሚ ቀውሱ ብዙ መንግስታትን እያሳሰበና ህብረተሰብአዊ እንቅስቃሴም ሊከሰት ይችላል በሚል ፍርሃት ውስጥ ገብተዋል። በብዙ አገሮችም አዳዲስ እንቅስቃሴዎች ተፈጥረዋል። በፈረንሳይ ብቻ ሰፊውን ወጣት ያካተተ የወጣቶች የፀረ-ካፒታሊዝም ፓርቲ ተቋቋሟል።

ይህ ዐይነቱ የዓለም ኢኮኖሚ ቀውስ እየገፋ በመጣበትና ብዙ አገሮችንም በማናጋት ላይ እያለ ካለፈው ስህተት ተምሮ ወደ ወስጥ ያተኮረ ፖሊሲ ከመከተል ይልቅ ለምን ወደ ውስብስብና ችግርን ሊፈታ ወደ ማይችለው ድርጅት አባል መሆን መጨቃጨቅ አስፈለገ? ከዚህ ጋር ተያይዞ ሰሞኑን በአንዳንድ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚስቶች የሚሰራጨው ፣ ኢትዮጵያ ስተክ ወይም የካፒታል ገበያ ያስፈልጋታል ፤ የዎል ስትሪት ተዋንያን ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቬስት ለማድረግ ዝግጁ ናቸው እየተባለ ነው። በእውነቱ እንደዚህ ዐይነቱ ኢኮኖሚስቶች የካፒታል ገበያ ያስፈልጋል ሲሉ በዚህ አማካይነት ወደ ተጨባጭ ኢኮኖሚው ላይ ሊፈስ የሚችል መዋዕለ ነዋይ ሊገኝ ይችላል ወይስ የቁማር መጫወቻ ይቋቋም ማለታቸው ነው። ነገሩ ግልጽ አይደለም። ከኬንያ እንደ ምንገነዘበው የናይሮቢ ስተክ ማርኬት እያለ እዚያው በዚያው በዚያች ከተማ ውስጥ ከአምስት በላይ የቆሻሻ(slums) መኖሪያ መንደሮች አሉ። ይህ ማለት አዲስ አበባ ስተክ ማርኬት ቢቋቋም ስራ ሳይሰራ ከኮምፒዩተር ጋር ሲታሽ የሚኖር አዲስ የህብረተሰብ ክፍል ከመፍጠር በስተቀር በምንም ዐይነት ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ሊያመጣ አይችልም። እነዚህ ኢኮኖሚስቶች ለአገራችን ዕድገት የሚያስቡ ከሆነ የባንኩን መስክ ለኢንቬስትሜንት በሚያመች መንገድ መዘጋጀት አለበት ብለው ለምን የተሻለ ሃሳብ አላቀረቡም? እንደሚመስለኝ በመንግስትም ሆነ በእነዚህ ኢኮኖሚስቶች የተያዘው ፈሊጥ ሌላ ፕላኔት ላይ ይኖሩ ይመሰል ፣ የዓለም ህዝብ ከእሳት ውስጥ እንዋጣ ብሎ ትግል ሲያደርግ ፣ አንተ ስተወጣ እኛ ገብተን እንቃጠልልሃለን ነው የሚሉት። ገብታችሁ ለመጋየት መብት አላችሁ ፤ ኢትዮጵያችንን ግን ለቀቅ አድርጉልን እንላቸዋለን።

ፈቃዱ በቀለ

## <u>ማሳሳቢያ ፤</u>

1ኛ) ተቃዋሚ የሚለው በፖለቲካ ተደራጅተው እንታገላለን የሚሉትን ብቻ የሚመለከት ነው። ይህ ፀሀፊ በፖለቲካ ሳይደራጁ ካለምንም ዕርዳታ ወርቅ ወርቅ ጽሁፎችን የሚያወጡና ለአገራቸው የሚቆረቆሩ ምሁራን እንዳሉ ያውቃል።

2ኛ) ከኒዎ-ሊበራሊዝም በአሻገር በሌላ መልክ ለመታገልና እየገፋ የመጣውን አዲስ አገር አፍራሽ ኃይል ለመቋቋም በሌላ መልክ መደራጀትና ሃሳብ ለሃሳብ መለዋወጥ የጊዜው አንገብጋቤ ጥያቄ ነው። እንቅስቃሴው በሳይንስና በስልጣኔ ላይ የተመረኮዘ ሲሆን አመጽን  አጥብቆ የሚቃወም መሆን አለበት።

3ኛ) ወደ ፊት በጋራ ተደራጅቶ አንድ በየወሩም ሆነ በየሶስት ወሩ የሚወጣ መጽሄት ማዘጋጀት የሚችል መሆን አለበት። መጽሄቱ የተፈጥሮ ሳይንስን ፣ የማቲማቲክስን ፣ የኢኮኖሚክስንና ሌሎች የማህበራዊ ሳይንስ ጽሁፎችን ፣ የአርኪቴክቸርና በጠቅላላው ለስልጣኔ የሚያገለግሉ ጥናታዊ ጽሁፎችን ያዘለ ቢሆን ይመረጣል።

4ኛ) አንድን መጽሄት ለማዘጋጀት ሙሉ ጊዜን መሰዋት ያስፈልጋል። በግማሽ የሚሰራ ስራ የለም። ስለዚህም ከፍተኛ ዝግጅትና ኃላፊነት የሚጠይቅ እንደመሆኑ መጠን ትብብር ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን ብቻ ታሪካዊ ኃላፊነትን መወጣት ይቻላል።